የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

**OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፯
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No 77
ADDIS ABABA, 3th August 2017.

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፵፮/፪ሺ፱ ዓ.ም
ለአነስተኛ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሊዝና የብድር አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈፃሚያ የሚውል ከአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ ለማግኘት የተፈረመ የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ገፅ ………………………………... ፱ሺ፰፻፳፪

**CONTENT**

Proclamation NO.1046/2017
European Investment bank Loan Agreement for financing Leasing and Lending for SMEs project Ratification Proclamation
page …………………………………………………………..9822

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፵፮/፪ሺ፱

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለአነስተኛ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሊዝና የብድር አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈፃሚያ የሚውል ፸ ሚሊዮን ዩሮ /ሰባ ሚሊዮን ዩሮ / የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ መካከል ግንቦት ፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ እና ግንቦት ፲ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በሉክዘምበርግ የተፈረመ በመሆኑ ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፤-

## PROCLAMATION No.1046/2017

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENET BETWEEN THE GOVEREMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE EUROPEAN INVESTMENT BANK**

**WHEREAS** , a Loan Agreement ,between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the European Investment bank stipulating that the European Investment bank provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 70,000,000 Euro ( seventy million Euro ) for financing leasing and landing for SMEs project was signed in Addis Abeba on the 16th day of May 2017 and in Luxembourg on 18th day of May 2017 ;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Loan Agreement at its session held on the 5th day of July 2017;

**Now, therefore,** in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

፩. **<u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለአነስተኛ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሊዝና የብድር አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈፃሚያ የሚውል ከአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ ለማግኘት የተፈረመ የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፵፮/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **<u>የስምምነቱ መጽደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአውሮፓ ኢንቨስትመንት ባንክ መካከል ግንቦት ፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ እና ግንቦት ፲ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በሊክዘምበርግ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር FIN° 85755 በዚህ አዋጅ ፅድቋል ፡፡

፫. **<u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፸ ሚሊዮን ዩሮ /ሰባ ሚሊን ዩሮ /በብድር ስምምነቱ በተመለከቱ ሁኔታዎች መሰረት በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. **<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፯ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ሙላቱ ተሾመ (ዶ/ር)**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፕሬዚዳንት**

1. **<u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "European Investment Bank Loan Agreement for financing Leasing and Lending for SMEs project Ratification Proclamation No.1046/2017".

2. **<u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement FIN° 85755 Signed in Addis Ababa on the 16th day of May 2017 and in Luxembourg on the18th day of May 2017 Between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the European Investment Bank is hereby ratified.

3. **<u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount 70,000,000 Euro (seventy million Euro) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force upon publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, on this 3th day of August 2017.**

**MULATU TESHOME (DR.)**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL**
**DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**